# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሣን *

ቅጽ 44 ቁ.2 ሰኔ 2016


## ዛሬ ላይ ሆነን ነገን እናልም!

በኢትዮጵያችን ለብዙ ዘመናት ሥር ሰዶና ተስፋፍቶ የኖረው ጉልተኛው የዘውድ አገዛዝ ሥርዓት እንዳበቃ በሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልተተካም። በመሆኑም የመንግሥት ሥልጣን በሕዝብ እጅ አልገባም። እስካሁንም ድረስ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑም አልተረጋገጠም። ዛሬም እንደጥንቱ ፍጹም የሆነ የፖለቲካ መብትና ሥልጣን ያለው በአገዛዙ እንጂ በሕዝብ እጅ አይደለም። በአገራችን የፖለቲካ ሥልጣንንና የዴሞክራሲ መብትን ለሕዝብ ለማድረግ የመሠረታዊ ለውጥ ጉዞ ከተጀመረ እነሆ 44ኛ ዓመቱን አስቆጥሯል። እየጋለና አንዳንዴም እየቀዘቀዘ የሚጓዘው ይህ የለውጥ እንቅስቃሴ አሁንም እንደቀጠለ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ታሪክ በተደጋጋሚ እንደታየው በጉልበት ሥልጣን የመጨበጥ ዘይቤ ከዘውዱ ሥርዓት ጋር አብሮ አፈር ለብሶ አልተቀበረም። በመሣሪያ ኃይልና በጉልበት ከመንግሥት ሥልጣን መወገድ ዛሬም እንደ ጥንቱ ሕያው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። የወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ሁኔታ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝብ ባፀደቀው ሕገ-መንግሥት ላይ የተመሠረተና የተዋቀረ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትና ሥርዓት ገና አልተፈጠረም።

በጠብመንጃ ኃይል የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው ጠባብ በሂረተኛና ጎጠኛው ቡድን ሁሉንም የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ መብት ጠቅልሎ በመያዙ ሕዝቡ ከሁሉም የፖለቲካ መብቶች ተገሏል። በሕይወቱ፣ በጉልበቱና በንብረቱ የሚያዝበት፣ ከዚያም አልፎ በአገሪቱ ማንነትና ምንነት ላይ ማንንም ሳያካትት ከሕዝበ-ውሳኔ ውጭ፣ በብቸኝነት የሚወስነው ህወሓት/ኢህአዴግ ብቻ ሆኗል። የህወሓት/ኢህአዴግ ሥርዓት የአንድ ፓርቲና

የአንድ ቡድን አገዛዝ ነው። የአስተዳደር መዋቅሮችና አውታሮች ሁሉ በአገዛዙ ካድሬዎች፣ በተለጣፊዎችና የጥቅም ተገዥዎች ቁጥጥር ሥር የዋሉ ናቸው።

በሕግ አውጭው፣ በሕግ ተርጓሚውና በሕግ አስፈጻሚው ክፍሎች መካከል በሕግ የተጠበቀና የተከለለ የሥልጣን ነፃነትና ክፍፍል ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም። የህወሓት ሥነ-ባሕሪ ሲስተዋልም ለወደፊቱም አይኖርም። ሁሉም በፓርቲው የሚሰየሙና የሚመሩ ስለሆኑ ተግባራቸው የፓርቲውን ፖሊሲ መቀበል፣ መደገፍና ሥራ ላይ ማዋል ብቻ ነው። ፓርላማው ፓርቲው የሚፈልገውን ሕግ መደንገግ፣ ፍርድ ቤቶቹ ፓርቲው የሚፈልገውን ፍርድ መስጠትና መወሰን፣ የመንግሥት ሠራተኞችም እንዲሁ ፓርቲው የሚፈልገውንና የሚወስነውን የግዴታ ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። የመከላከያና የፀጥታ ኃይሎችም ታማኝነታቸው፣ ታዛዥነታቸውና አገልግሎታቸው ለአገሪቱና ለመላው ሕዝብ ሳይሆን፣ ለጎጠኛውና ለጠባብ ብሄረተኛው የህወሓት ቡድን ነው። ይህ ዓላማው ፍጹም የተሟላ እንዲሆንለት በግላቸው፣ በነፃነት ራሳቸውን አደራጅተው በነፃ መንቀሳቀስ የሚፈልጉትን የብዙኃን ድርጅቶችንና ማኅበራትን ሳይቀር አዳክሞ፣ በታትኖና አፈራርሶ የፓርቲው ተቀጥላና ተለጣፊ በሆኑ ማኅበራትና ድርጅቶች ተክቷቸዋል። ለዚህም ድርጊቱ የተፈጸመባቸው ለነፃነታቸውና ለመብታቸው የሚታገሉ የሠራተኞች፣ የመምህራንና የጋዜጠኞች እንዲሁም ሌሎች የሙያ ማኅበራትና ድርጅቶች በዚህ አኳያ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። የሃይማኖት ተቋማትም ቢሆን ከዚህ ወረርሽኝ አላመለጡም። ቤተክርስቲያንና መስኪድ ከጥንት ጀምሮ ተከብረውና ተፈርተው የኖሩ የእምነት ቦታዎቻችን እንዳልነበሩ አሁን ተደፍረው በህወሓት/ኢህአዴግ መዳፍ ውስጥ ገብተዋል። ዛሬ ቄሱም፣ ጳጳሱም፣ ሸኹና ኢማሙም የሚሾሙትና የሚሻሩት በህወሓት/ኢህአዴግ ትዕዛዝና ፍላጎት ሆኗል።

በኤኮኖሚው መስክም እንዲሁ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ ይዞታ ምን እንደሚመስል በምልዓተ-ሕዝቡ ዘንድ ቁልጭ ብሎ የሚታወቅ ነው። በደርግ ዘመን የመንግሥት ንብረት የነበሩ ግዙፍ ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በህወሓት/ኢህአዴግ እጅ ወድቀዋል። በዋና ዋና የንግድ መስኮችም ቢሆን፣ የአገዛዙና ካድሬዎቹ ሌሎችን እያጉላሉና እያዳከሙ ባለንብረትነታቸውን አረጋግጠዋል። አገዛዙ እንደተቋም ከግለሰብ ነጋዴዎች ጋር "በመወዳደር" ከበርቴ ነጋዴ የሆነባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ናት ማለት ይቻላል። ነጋዴውም በቀረጥ፣ በቤት ኪራይና በመሳሰሉት ሽፋን ይዞታውን መጠበቅም ሆነ ማጣት የሚችለው በህወሓት ቅጥረኞች መልካም ፈቃድና ውሳኔ ብቻ ነው።

ገበሬው መሬት፣ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ማግኘት የሚችለው በአገዛዙ ካድሬዎች በሚመራው በገበሬ ማኅበር አማካኝነት ብቻ ስለሆነ፣ ሳይወድ በግድ በቁጥጥራቸው ሥር እንዲውል ተደርጓል። ካድሬው ካልፈቀደ ገበሬው በራሱ የመወሰን መብት የለውም። ስለሆነም ዛሬ ገበሬው ድሮ ወደነበረበት የጭሰኝነት ሥርዓት ተመልሷል ማለት ይቻላል። ከገበሬውና ከግል ተዳዳሪው ውጪም አብዛኛው ትምህርት ቀመስ ኃይል የሥራ ዕድል ማግኘት የሚችለው የህወሓት/ኢህአዴግ አባል ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሠራተኛ ከአገዛዙ ቁጥጥር ውጪ አይደለም ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ በአገራችን የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ይባስ ብሎም የእምነት ተቋማትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወትና ኑሮ በህወሓት/ኢህአዴግ ሁለንተናዊ ሥልጣን ሥር ወድቆ የሚገኝበት ጊዜ ነው። የሥልጣኑ ጥልቀትና ምጥቀት ገደብና ድንበር የማይገታው ፍጹም አምባገነን ሆኗል። ህወሓት/ኢህአዴግ ለ25 ዓመት ማለትም ለአንድ ትውልድ ዕድሜ፣ አገራችንን በአምባገነንነት ተቆጣጥሯታል። ባለፉት 25 ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያንን በጎሣ፣ በቋንቋና በክልል እንዲበታተኑ አድርጓል። ኢትዮጵያ በረዥም የአንድነትና የነፃነት ታሪኳ ያገኘቻቸው ዕሴቶች ሁሉ ተራክሰዋል፤ ስለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊነት መናገር ትምክህተኝነት ተብሎ ተፈርጇል። አርበኛው ተንቆ ከሃዲው ተከብሯል። ሀገር በቀል የሆኑ ማኅበራዊ ዕሴቶች ማለትም ማኅበር፣ ዕድርና ሰንበቴ እንዲበታተኑና እንዲፈርሱ ተደርገዋል። ኢትዮጵያውያን በየቀበሌው ቤታቸው እየፈረሰና እየተዘረፈ እንዲበታተኑ ሆነዋል። በሠፈራ ስም ከመሃል ከተማ እየተፈናቀሉ የገበያም ሆነ ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎት ወደማያገኙበት አካባቢ በግዳጅ ተወስደዋል፣ በመወሰድ ላይም ይገኛሉ። ደሃውን አፈናቅለው መሀል ከተማው ውስጥ ቱባ ባለሥልጣናት ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ሠርተዋል፣ እየሠሩም ይገኛሉ። በኢትዮጵያዊነት ፍትህ ማግኘት የህልም እንጀራ ሆኗል። ጉልበት ያላቸው ወጣቶች እየተሰደዱ የባህርና የበረሃ እራት እየሆኑ ነው፣ ጧሪና ደጋፊ ያጡ በዕድሜ የገፉ አረጋውያን መጠለያ አልባ ሆነዋል። ሀገራችን ከፍተኛ የውጭ ዕዳ ተሸካሚ ሆናለች። በልመና፣ በስጦታና በዕርዳታ የሚገኙ ቆሳቁሶች ቅድሚያ ለህወሓት/ኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ተከፋፍለው የተረፈውን ሕዝቡ ከአቅሙ በላይ የሆነ ገንዘብ እየከፈለ እንዲገዛ ይገደዳል።

የሕዝብ ብሶት የወለደው እምቢተኝነት ህወሓት/ኢህአዴግንም ጊዜውን ጠብቆ መለብለብ ጀምሮታል። ቀደም ሲል የአዲስ አበባ ማስተር ፕላንን ተንተርሶ በአዲስ አበባና አካባቢው የተጀመረው አመፅ አብዛኛውን የኦሮምኛ ተናጋሪ አካባቢን አነቃንቆታል። በማንነት ላይ ተመሥርቶ በወልቃይት ጠገዴና በጠለምት የሕዝብ መነሳሳት የህወሓትን ቀልብ

እየገፈፈው ነው። በጋምቤላ፣ በኮንሶ፣ በአርባ ምንጭና በኦጋዴን እየተቀጣጠለ ያለው አመፅም ህወሓትን እያመሰው ይገኛል። በጎንደር አካባቢ ከአገዛዙ ጋር ተፋጦ ያለው ሕዝብ የህወሓት ግፍና በደል ትከሻው መሸከም ያቃተው የመልካም አስተዳደር እጦት ያንገፈገፈው አርሶአደር ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ እንዳለፉት 25 ዓመታት በዘፈቀደ ለመግዛት፣ ኢትዮጵያውያንም እንዳለፈው ላለመገዛት ግብግብ የተጋጠሙበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል። ስለሆነም ኢትዮጵያ መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ላይ ከ44 ዓመታት በፊት የተጀመረው የኢትዮጵያ የመሠረታዊ ለውጥ እንቅስቃሴ በአሁኑ ፈታኝ ወቅት እንዴትና ወዴት እያመራ ይሆን? የሚለው ጥያቄ ሕልውናን ያማተረ ዓቢይ ጥያቄ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንክሮ የሚመለከተው ነው። አሁንስ ወዴት? አዎ! ወዴት?

አገራችን የዓለምአቀፍ አካል በመሆኗ በወቅቱ የሚታየው ዓለምአቀፋዊና የአካባቢ ሁኔታዎች በአገራችን ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። በአሁኑ ወቅት በሁኔታው አመቺነት ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈልጉ ኃይሎች በየአቅጣጫው የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉ ነው። በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ የሚታየው ሁኔታ ለአገራችን በይበልጥ አሳሳቢ መሆኑን ማጤን እጅግ አስፈላጊ ነው። ታሪካዊ የውጭ ጠላቶቻችን የውስጥ ተባባሪ ቡችሎቻቸውና አድርባይ ኃይሎች አጋጣሚውን ለመጠቀም የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ሲሯሯጡ እያየን ነው። በቀይባህር አካባቢ የውጭ ኃይል ለረዥም ዓመት የሚቆይ ውል ከኢሳያስ አገዛዝ ጋር መፈራረምና በጅቡቲ አካባቢ የተለያዩ ኃያላን መንግሥታት ጦራቸውን ማስፈራቸው ለወደፊቱ የኢትዮጵያን ፀጥታ የሚያሰጋ መሆኑ ግልጽ ነው። የአገራችን ታሪክ እንደሚያስረዳን ወራሪዎች አገራችን ለመቆጣጠር በተለያየ ጊዜ ሙከራ ያደረጉት በቀይባህር በኩል ነው። አሁንም በተለያየ መልክ ተቀያይረውና ረቂቅ ሆነው የመጡብን እነዚያው የጥንቶቹ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ናቸው።

<u>አገራችንን ከውድቀት የማዳኛው ጊዜ አሁንና አሁን ነው።</u> አንድነታችንና በነፃነት የረዥም ዘመን የመኖር ህልውናችን የታሪካችን በጎ ጎን ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያዊነታችን ዓይነተኛ መግለጫ ነው። በዚህ ወቅት የለውጥ ኃይሎች ማድረግ የሚገባቸው ጥንቃቄ አለ። ህወሓት/ኢህአዴግ በደደቢት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የራሱን አገዛዝ ለማስፈንና እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ስሜትንና ኢትዮጵያውያንን ለማዳከም በሕዝባችንና በአገራችን የዘራው ነቀርሳ በግልጽ የሚታይ ነው። በአገዛዙ አባባል ቀደም ሲል በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የደረሰው በደል መንስዔው በጊዜው የነበረው ሥርዓት-መንግሥት የአሠራር ጉድለት ሳይሆን የአማራው ብሄረሰብ ያስከተለው በደልና ጥፋት ነው በማለት የተዛባ

እይታን አናፍሷል። ይህንን ነቀርሳ የአገዛዙን አውታሮች ሁሉ በመጠቀም በሰፊው በማሰራጨቱ የአገራችንን ህልውና ከሚፈታተንበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በመሆኑም ይህንን አገር አጥፊ ቅስቀሳን ተቋቁሞ የሀገራችንን ታሪክ ለትውልድ በትክክል ለማስተላለፍ እንዲቻል የኢትዮጵያውያን ሁሉ ተግተው መሥራት አለባቸው እንላለን።

የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከተወገደ በኋላ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅመውን አዲስ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመዘርጋትና የመደብለ-ፓርቲን አሠራርና ዘይቤ እውን ለማድረግ የሽግግር መንግሥትን ማቋቋም የግድ ይላል። በሽግግር መንግሥት ወቅትና ሂደት ላይ በፓርቲ ያልታቀፉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአገሪቷ መሠረታዊ ጥያቄዎችና የወደፊት ዕድል ላይ የመሳተፍና፣ የመወያየት መብት ይኖራቸዋል። በዚህ ረገድ የሚያደርጉት ተሳትፎና አስተዋጽዖ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት ለሚደረገው ጥረት ሕዝባዊ ይሁንታን ለማግኘትም ይረዳል። በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከፖለቲካ የተገለሉና የታገዱ ኃይሎች ሁሉ በሽግግር መንግሥት ውስጥ በመሳተፍ አቋማቸውን አስመልክተው የመከራከር፣ የመወያየትና ወደ ጋራ ስምምነት የመድረስ ዕድል ያገኛሉ። የእነዚህ ዓይነት ቡድኖችና ኃይሎች በሽግግር መንግሥት ውስጥ መካተትና መሳተፍ በሀገሪቱ ላይ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ይረዳል። የዕድገትና የልማት ፕሮግራም ያለአንዳች ሁከትና ጦርነት በቀጣይነትና በዘላቂነት ለመተለምና ለማካሄድ ያስችላል። በዚህ ወቅትም በህወሓት/ኢህአዴግ አፈና ነፃነታቸውና ህልውናቸው የተደፈረና የተገሰሱ የሙያና የሲቪክ ድርጅቶች እንደገና ነፍስ የሚዘሩበትን ዕድል ያገኛሉ። ሙሉ ለሙሉም በሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል።

ስለዚህ የመደብለ-ፓርቲ ሥርዓት ፈር ይዞና ተጠናክሮ ሥር እንዲሰድ ዴሞክራሲያዊ መዋቅሮችን ለመዘርጋትና ለማዋቀር ለሚደረገው ዝግጅት የተቀናጀ የሽግግር መንግሥት ሂደት ወሳኝነቱ አጠያያቂ አይደለም። የሽግግር መንግሥት ምሥረታን እውን ለማድረግ በተናጠል ሳይሆን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታገሉ ኃይሎች ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊታገሉለት የሚገባ ዓላማ መሆኑን በማመን ኢሕአፓ (አንድነት) ከዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመሥራትና የድርሻውን ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን ያረጋገጣል።

ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ በጋራ እንታገል!